**ኢትዮጵያዊነት፡- *የዜጎች መብት ማስከበሪያ ጉባኤ***

**ETHIOPIAWINNET:*COUNCIL FOR THE DEFENSE OF CITIZEN RIGHTS***

***www.ethiopiawin.net***

**ECDCR P.O Box 171, East Lansing, MI 48823**

## ግልፅ ደብዳቤ

## ይድረስ ለኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት

**03/15/2019**

ባለፉት ሁለትና ሦስት ዓመታት ወጣቶችና ሁሉም የኅብረተሰብ ክፍሎች ከጫፍ እስከጫፍ ተነቃንቀው ባደረጉት ከፍተኛ የመብት ተጋድሎ ወደ ሕግ የበላይነት፣ የዕርቀ ሰላም፣ ሃገራዊ አንድነትና ወደ ዜግነት ፖለቲካ የሚወስዱ የማይናቁ ድሎች ተገኝተዋል። ሆኖም ይህ የብዙ ዜጎችን ሕይወት የቀጠፈ ለውጥ፣ ለውጡን በሚጠሉ በኛ መንገድ በቀር ወይም ለኛ ብቻ ካልሆነ በሚሉ ጽንፈኛ ኃይሎች እየተቦረበር ይገኛል። ምንም እንኳ ለውጥ አልጋ ባልጋ የሚሄድ አለመሆኑን ብንገነዘብም፣ አሁን በሀገራችን የምናየው ሁኔታ በተደራጀና በሰከነ ሕዝባዊ ንቅናቄ እንዲመራ ሆኖ የአክራሪ ጽንፈኞች ድንፋታ ካልተገታ፣ ቀድሞ ከነበርንበት ወደ ከፋ መከፋፋልና አላስፈላጊ ግጭት የሚወስድ፣ የዜግነት መብትንም ወደሚደፈጥጥ አስከፊ አቅጣጫ እንደሚሄድ ግልፅ ነው። ይህ በየአካባቢው ቦግ እልም የሚል ግጭትና መፈናቀል ከቀጠለ እስካሁን በሩዋንዳ፤ ሶሪያ፤ የመንና ሶማሊያ ውስጥ ካየናቸው ያላነሰ የመጠፋፋትና የመገዳደል ቀውስ ውስጥ እንደሚከተን መታወቅ አለበት። የሀገራችን ቀውሶች መሠረታዊ መንሣኤዎች በሕገ መንግስቱ ላይ የተገለፀውና የተዋቀረው የብሔር ፖለቲካና፣ በቋንቋ ላይ የተመሠረት የክልል አስተዳደር መሆኑን ብናውቅም፤ በመንግሥት በኩል የሕግ የበላይነትን ለማስፈን የሚታየው ለዘብተኝነት ከሚመስል ከልክ ያለፈ ትዕግስት በሃገሪቱ ለሚታየው የሕዝብ የዕለት ተዕለት መፈናቀል፤ መሰደድ ረሃብና እና እንግልት እንዲጭምር አድርጎታል። ችግሩና ቀውሱ የሚገለጠው በተለያዩ መንገዶች ነው፤

**1ኛ/ ሕገ መንግሥቱ የየአካባቢውን ብሔር ክልላዊ ባለቤትነት ያረጋገጠ እንጂ በክልሉ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንን መብት በማያሻማ ሁኔታ አይገልፅም። ይህም የአካባቢው ብሔር/ብሔሮች ተብለው ከተጠቀሱት ውጭ ያሉ በክልሉ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ዜጎችን መብት ለመጣስ መንገድ ከፍቷል።**

ባለፉት 27 ዓመታት ሕዝብ ተውልዶ ካደገበት ወይም ከኖረበት ቀየው የብሔር ማንነቱ ከሌላ አካባቢ በመሆኑ ብቻ የዜግነት መብቱ ተገፎ ፤ ንብረቱን ተቀምቶ፤ ባዶ እጁን ከአካባቢው እንዲወጣ ተደርጓል። ይህ ደቡብን፣ ኦሮሚያን ቤንሻንጉልን፣ ጋምቤላን ፣ ሱማሌና አማራ ክልሎችን ሲያካትት ክቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ብዛቱም አስከፊነቱም እየተበራከተ መጥቷል።

ባሁኑ ሰዓት የጌዴዎ ወንድሞቻችንና እህቶቻችን የረሃብ ድምፅ እያሰሙ ሲሆን ከ50,000 በላይ ይገመታሉ አንዳንዶችም እስከ 800,000 ያደርሷቸዋል። እነዚህ በጎሳ ፖለቲካ ምክንያት ከጉጂ ዞን ተፈናቅለው የሚሰቃዩ ወገኖቻችን ምስላቸው የከሳ፣ በረሃብ የጠወለጉ፣ ያለመጠለያ እየተሰቃዩ እያለ በሠላም የመኖር ዋስትናቸው ሳይረጋገጥ ተፈናቅለው ወደመጡበት ወደየቤታቸው ተመለሱ ይባላሉ። ከክልሉ እርዳታ እንዳናገኝ ተከልክለናል በማለት ምሬታቸውን እንደገለፁና፣ የግብረ ሠናይ ድርጅቶችም

እንዳይደርሱላቸው ክልሉ እገዳ በማድረጉ ዕርዳታ እንዳናገኝ ተከልክለናል ማለታቸውንም ሰምተን እጅግ አዝነናል። በዚህም ምክንያት ለኢትዮጵያውያን ወገኖቻቸው የድረሱልን ጩኸት እያሰሙ እንደሚገኙም ተረድተናል። አሁን ጉዳዩን ዓለም አቀፉ ማህበረ ሰብ ዘንድ እየደረሰ ነው። https://www.theguardian.com/global-development/2019/mar/14/shadow-falls-over-ethiopia-reforms-warnings-of-crisis-ignored-abiy-ahmed?CMP=share_btn_tw .

በመንግሥት በኩል ለዚህ ተደጋጋሚና አሳሳቢ ለሆነው በተለያዩ ክልሎች ለሚከሰተው የዜጎች መፈናቀልና ለስቃይ መጋለጥ ዘላቂ መፍትሄ ለመስጠት መንስዔ የሆነውን በሕገ መንግሥቱ ስለ ብሔር/ብሔረሰቦች በዘርና በቋንቋ እንዲከለሉ ያስቀመጠውን ሕግ እንደገና ለማየት እየሞከረ እንደሆነም እናውቃለን። ይህ እስኪሆን ግን መንግሥት ዜጎች እየተሰቃዩ መሆኑን ተገንዝቦ የሌሎች የውጭና የውስጥ ዕርዳታ ሰጪዎችንም በማሳተፍ፣ መጠለያ፣ ምግብና መድሃኒት በማቅረብ በአስቸኳይ እንዲደርስላቸው እያሳሰብን ሰባዊነትንም በማስቀደም ያካባቢ ካድሬዎች ከዕርዳታ እገታ ተግባራቸው እንዲቆጠቡ እንጠይቃለን።





***ከጉጂ ዞን የተፈናቅሉ ጌዴኦ ወገኖቻችን***

በተመሳሳይ ሁኔታ ከቤንሻንጉል የተፈናቅሉ ወገኖቻችን ሁኔታ እንደዚሁ እጅግ አሳዛኝ ነው። እነኝህን ወገኖቻችን አገር ቤት ድረስ በመምጣት የጎበኘናቸው ጥር ወር፣2011 ዓ. ም. መጀመርያ ነበር። በሺዎች ይቆጠራሉ። ዓባይ ማዶ ከተሰኘ ቦታ ወና ቤት ውስጥ እንደ እንስሳ ባዶ ስሚንቶ ላይ ያድራሉ ይውላሉ። እንደተመለከትነው በቁጥር ህፅናት ልጆች፣ እናቶችና ወጣቶች ይበዛሉ። የረባ ንብረትም ሆነ ቁሳቁስ የላቸውም። ጉዳዮ ከሚመለከተው የክልሉ የርዳታ ክፍል ባልደረባ ለመረዳት እንደቻልነው በመጠለያው ውስጥ ከሚገኙት ከ3,000 ሰዎች መካከል ብርድ ልብስ ያገኙት 300 ብቻ እንደሆኑ ነው። ለዚያውም አንድ ብርድ ልብስ ሶስት ወይም አራት ቤተሰብ ላለቸው ብቻ ነው የታደለው። እንደተመለከትነውም

ሰውነታቸው የተጎሳቆለ ነው። የደረሰባቸውን ሰቆቃ ሲነግሩን ሕይወታችንን  ያተረፍነው የሞተው ሞቶ የተረፍነው በዱር ተሸሽገን በስንት መከራ እዚህ ደርሰን ነው ብለውናል።

ጨምረውም “በቤኒሻንጉል አማራ ወይ ኦሮሞ ብትሆን ምንም መብት የለህም፤ እንደሰው አንታይም፤ ከእንስሳ በታች ሆነን ነው የምንታየው። መሣሪያ አይፈቀድልንም። ዱላ እንኳን ብንይዝ ምን አስበህ ነው እንባላለን። አቤቱታ ብታሰማ የሚሰማህ የለም፤ አንተ መጤ ነህ፤ ካልፈለክ አገር ልቀቅ ትባላለህ። ሁለተኛ ዜጎች ነን።” ምን እየሆን ነው? የጎሰኝነት እብደት እንጅ! በማለት ሰቆቃቸውን አካፍለውናል።

በኢትዮጵያ ውስጥ በገዛ ሀገሩ የተፈናቀለ ሕዝብ ከሁለት ሚሊዮን ተኩል በላይ መድረሱ ይነገራል። ይህ ቁጥር በመፈናቀልና በማፈናቀል ብዛት በዓለም አንደኛ አድርጎናል። ይህ የጎሰኝነት እብደት ካልተባለ ሌላ ምን ሊባል ይችላል? ይህ ሁሉ ሕዝብ በሚፈናቅልበት ጊዜ ከቁጥሩ ባሻገር የንብረት መውደም፤ የአካል ጉዳትና መገደል ያለምግብና መጠለያ መቅረት፤ ለተለያዩ በሽታዎች መጋለጥን ሁሉ ያስከትላል።





*ከቤንሻንጉል የተፈናቅሉ ወገኖቻችን*

መፈናቀሉ በክልሎች ብቻ የተውሰነ ሳይሆን በከተማዎችም በሰፊው እየተካሄደ ይገኛል። ቦታው ለልማት ይፈለጋል፣ ሕጋዊነት የሌለው ግንባታ ነው በሚል፣ ከአዲስ አበባ በብዙ ሺህ የሚቆጠር ህዝብ በየጊዜው ያለበቂ ካሣ ተፈናቅሏል። የቁጥር ጉዳይ እንጂ በሁሉም የክልል ከተሞች በተመሳሳይ ግፍ ሲፈጸም ታይቷል። ለዋቢነትም የቡራዩን፤ የለገጣፎ/ለገዳዲ፤ የአማሮ፤ የዬም፤ የጌዴኦ በቅርቡ ደግሞ በዘዴ እየተስተባበለ ያለው የቄለም መፈናቀል ልብ ይሏል። አቤቱታው ግን አልተሰማም፤ ተሚጋች ወገንም አላገኘም።  የሰሞኑ በለገጣፎ የተደረገው "ሕገ ወጥ" ቤት የማፍረስ እርምጃ  የቤተሰቦችን የኢኮኖሚ ሁኔታ፣ የለውጡን ሰብዓዊነት ይዘት፣ የዜግነት ክብርን፣ ጊዜያዊ የሽግግር ጊዜ መጠለያ ዕቅድን ባላስተዋለ መልኩ፣ ጥረው ግረው የሠሩትን የመኖሪያ ቤቶቻቸውን አፍርሰው፣ ቤተሰቦቻቸውን ያለመጠለያ ማስቀረት፣ ከሰብዓዊነት ውጭ ነው። ይህ አስከፊ አድራጎት ደግሞ የሚካሄደው በተዋረድ በመንግሥት ትዕዛዝ በሚሆንበት ጊዜ ችግሩን የበለጠ የከፋ ያደርገዋል።

የሰብዓዊ መብት ጥሰትና የአስተዳደር ብልሹነት መንግስትን በየደረጃው የሚያስጠይቅ ጉዳይ ነው። የተባበሩት መንግሥታት የሰዎች “ምግብና መጠለያ ማግኘት የተፈጥሮ መብታቸው” ነው የሚለውን

ድንጋጌም የሚጥስ ነው። ይህ በገጠርም ሆነ በከተማ ሕዝብን የማፈናቀል ተግባር በሕግ የበላይነት ላይ የቆመ መንግሥታዊ ሥርዓት እስኪመሠረት ድረስ፣ **መንግሥት ዜጎችን ማፈናቀልን የሚያስቆም የእገዳ ውሳኔ ማሳለፍ (Moratorium) ይገባዋል።**

**2ኛ/ ወቅታዊው አተራማሽ - የአዲስ አበባ ጉዳይ፣**

አዲስ አበባ የተገነባችውም ሆነ መቀመጫቸውን በከተማዋ መሥርተው የሚኖሩ ከመላው ኢትዮጵያ ከመጣ ሕዝብ ነው። ከተማይቱ አሁን ባለው ሕገ መንግሥት የራሷ የውስጥ አስተዳደር ያላት የፌደራል መንግሥቱ አካል ናት። በቅርቡ የብሔር ፖለቲካ አቀንቃኞችና አንዳንድ የኦሮምያ ክልል ባለሥልጣኖችን ጨምሮ የዜግነት መብቶችን በሚጥስ መልኩ ከፍተኛ የሆነ 'አዲስ አበባ የኛ' የሚል መፈክር አንግበው የባለቤትነትና የልዩ ጥቅም ጥያቄ ቅስቀሳ ሲያካሂዱ አስተውለናል።

በሕግ አስከባሪ ክፍልም ዜጎችን እኩል እንደማይመለከት የሚያሳብቁ ክስተቶችንም የተፈናቀሉ ዜጎች ወይንም በሰላም የዲሞክራሲ መብታቸውን ተጥቅመው በተፈቀደ ሠላማዊ ሰልፍ ድምጻቸውን አሰምተው በሰላም የተመለሱ ወደ እስር ቤት ሲጋዙ የተፈናቀሉት ለእንግልት መዳረግ ትክክል አይደለም። ሌላው አስገራሚው ነገር እኒህ ቅስቀሳዎች የሚደረጉት ሕገ መንግሥቱ ሁሉን ዜጎች እኩል ማየት እንዲችል የሃሳብ ልውውጥ በሚደረግበት ዋዜማ ላይ መሆኑ ነው። በእኛ እምነት በአዲስ አበባ "ባለቤትነት" ጉዳይ የተነሳው ጥያቄ አጣዳፊ አይደለም። ከሱ በላይ አስቸኳይና አንገብጋቢ የሕዝብ ጥያቄዎች የሚስተናገዱበትና ወቅቱን ጠብቆ ፣ በፅሞና በውይይት ሊስተናገድ የሚችል ጉዳይ ነው ። ይህ ሕገ መንግሥት በዜጎች ሙሉ ዲሞክራሲያዊ ተሳትፎ እስኪሻሻል ድረስ መጠበቁ አስፈላጊ ነው። የቀረበው ጥያቄ ባለው ሕገ መንግስት በፍትሃዊነት የሚስተናገድ አለመሆኑን መንግሥት አቋሙን በቁርጠኛነት ለሕዝብ መግለፅ አለበት። ይህን አለማድረግ ግን በአብዛኛው የለውጡ ደጋፊወች ዘንድ የተፈጠረውን ጥርጥሬ ማጠናከር ይሆናል።

ዜጎችም የዜግነት መብታቸው እንዲጠበቅ ከፍተኛ የሆነ ሰላማዊ ንቅናቄ ማድረግና መታገል ይጠበቅባቸዋል። ንቅናቄው ሕጋዊ ተጠያቂነት ባለው ተቋም በዲስፕሊን መመራትም ይኖርበታል።

**3ኛ/ ጥያቄ ማቅረብ መብት ነው፣**

ማንኛውም ሕዝብ ወይም ግለሰብ በማንኛውም ጥያቄ ላይ ቅሬታውንም ሆነ የሚፈልገውን ነገር በሰላማዊ መንገድ መግለፁ መብቱ ቢሆንም፣ ቆንጨራ ዱላና ገጀራ ይዞ ሰልፍ መውጣት የሚሰጠው መልዕክት፤ የተጠየቀው ጥያቄ ካልተመለሰ ቀጣዩ የኃይል እርምጃ መውሰድ መሆኑን የሚጠቁም ነው። መሣሪያ ይዞ ሰልፍ መውጣት ሕጋዊነት አይደለም። ነገ ሌላው ጠመንጃ ይዞ ቢሰለፍ ጥያቄው ወደ ግጭት የሚወስድ ስለሚሆን መንግሥት በማያወላውል ሁኔታ ሕጉን ማስከበር አለበት።

4ኛ/ የወጣቶች ስርዓተ አልበኝነትና የመንግስት ቸልተኝነት፣

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ባንዳንድ አካባቢዎች ያባት የናቶቻችን ባህል ያልሆነ፣ ሰባዊነት የሌለው፣ ጭካኔ የተሞላበት የንብረት ዘረፋ፣ ብሔር ተኮር ስድብ፣ ድበደባ ሌላም ሌላም ይስተዋላል። ይህ የሚደረገው በተደራጁ ወጣቶች አማካይነት ነው። አንዳንዴ "ቄሮ" ነን እያሉ የመልካሙን የኦሮሞ ወጣት ንቅናቄ ስም ለማጠልሼት ይጠቀማሉ። ሌላ ጊዜ ማንነታችውን አይናገሩም። ይህ አካባቢ የኛ ነው፣ ከሀገራችን ውጡልን ማለትን ያበዛሉ። ጉዳዩ በሐረሪ ክልል፣ ቤንሻንጉል፣ ድሬዳዋ፣ ሐዋሳ፣ በቅርቡ ደግሞ በቄለም ወለጋ ተከስቷል። አቅም ከማነስም ይሁን "ወጣቱን" ከመደገፍ ፣ የየአካባቢው ፖሊሶች ሕግ አያስከብሩም። ብሔራዊ መንግስትም ጉዳዩን ቢያውቅም ቸልተኛ በሚያስብል መመልከት የመረጠ ይመስላል። ወጣቶች ያገኙትን ነፃነት ለማጣጣም ገና ትምህርት አላገኙም። ይህ ቦዘኔያዊ ህገወጥነት ሊገታ የግድ ነው። ለዚህም የመንግስትና የማህበረሰቡ መሪዎች ጣልቃ ገብነት አስፈላጊ ነው።

ያለነው በሽግግር ወቅት ላይ ነው። ሁሉም ነገሮች አልጋ ባልጋ እንደማይሆኑ ይታወቃል። መንግስት ሁሉን ጉዳይ መፍትሄ የመስጠት ችሎታ አለው ብለን አንገምትም። ግን ቢያንስ የህዝብን የዕለት ፀጥታና ደህንነት ላይ አትኩሮ ሊሰራ ይገባል እንላለን። ለዚህም ህዝብን ማሳተፉ ይጠቅማል። ፍትሀዊ ሥርዓት ለመትከል የሚደረጉት እንቅስቃሴዎች በፊታችን የተጋረጡትን ቅድሚያ ሰጥቶ በመፍታት መጀመር ያስፈልጋል።

ለሕዝብ መብቶች መከበር በትጋት እንስራ !

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!